የረቡዕ ጥቅምት 16 1998 ዓም ( የኦክቶበር 26 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## የጦርነት ነገሪት መኅሰም
## የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ አይለውጠውም

"የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ" የሚባለው ባህላዊ እሴት በትክክል ሊተረትበት የሚችል ክፍል በዛሪይቱ ኢትዮጵያ ሊኖር ቢችል፥ መለስ ዜናዊ ብቻ ነው። በተደጋጋሚ ይህ የብልጣ ብልጥነት ፖሊቲካው የያዘለት ስለሚመስለው፥ ዘወትር የጦጣ ሽምጠጣውን የአገዛዙ ዓይነተኛ ዘዴ አድርጎት ቆይቷል። ለአለፉት አስራ አራት ዓመታት፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ቻይነት፥ እንደ ግዴለሽነት፥ ትዕግስቱን እንደ ፍርሃት፥ አስተዋይነቱን እንደ ሞኝነት፥ ሀገር ወዳድነቱን፥ እንደ ተላላነት ቆጥሮ ተጠቅሞበታል።ለተወሰነ ምዕራፍም ሰርቶለታል ማለት ይቻል ይሆናል። ይህ ግን እስከ ማዕዜኑ ሊቀጥል አይችልም። አንድ ቦታ፥ አንድ ጊዜ ሊቆም ይገባዋል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት፥ መለስና ኢሳያስ በአካሄዱት የሁለት ዓመታት ትርጉም የለሽ ጦርነት የጠፋውን የሰው ሕይወትና የወደመውንም ንብረት ሁሉም ዜጋ ስለሚያውቀው በዚያ ላይ ትኩረት ማድረጉን እንተወዋለን። እናተኩር ካልንም፥ ልባችን ይደማ እንደሁ እንጅ መፅናናትን አይሰጠንም። ዛሬ ያ አውዳሚ ጦርነት ያስከተለውን የታሪክ ጠባሳ ከሚያሳዝነው የታሪክ ማኅደራችን ውስጥ አቆይተን፥ አሁንም ወደሌላ አውዳሚ ጦርነት ሊከተን በሚኅሰመው የዕልቂት ነጋሪትና ይህን በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች ላይ የሚያመጣው አሰቃቂ ጦርነት ለማቆም ምን መደርግ አለበት? በሚለው ጉዳይ መነጋገሩን መርጠናል። ጦርነቱ ተገባደደ ከተባለበት ወቅት አንስቶ እስካሁን ድረስ፥ በአካባቢው አንፃራዊ ሠላም ነበር ሊባል ቢችልም፥ በኢትዮጵያ ሀገራችን ግን ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ አያውቅም። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለመላቀቅ የሞት–ሽረት ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል። በአዕላፍ የሚቆጠር ዜጋ ዕንበለ–ፍርድ በአሰቃቂው የወያኔ ወኅኒ ቤቶች በመሰቃየት ላይ መሆኑ ለማንም ስውር አይደለም። ይህን መሪር አገዛዝ በመቃወም ሀገሩን እየለቀቀ የሚሰደደውን ዜጋ ቁጥር ማወቅ የሚቻል አልሆነም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥በርሀብ ፥ በበሽታ፥ በድኅንት፥ በኤድስ ተውሳክ፥ በኢኮኖሚ ድቀት፥ በፖሊቲካ መናወጥ፥ በአለመረጋጋት፥ በውጥረትና ጭንቀት በዓለም ደረጃ የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል፡ ይህ ደግሞ በሃያ አንደኛው ምዕተ–ዓምት ለሚኖር ሕዝብ የህይወት መስፈርት ሊሆን አይችልም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ የተሰጠው ዕድል ፋንታው ነው እስካልተባለ ድረስ።

ወቅታዊው የሀገራችን የፖሊቲካ ሀቅ የሚናገረው፥ በሕዝቡና በአገዛዙ መካከል የሞት ሽረት ትግል እየተካሄደ ያለ መሆኑን ነው። ከአለፈው የግንቦት ወር ጀምሮ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መለስንና ገብረ-አበሮቹን በድምፁ ከሥልጣን አስወግዷቸዋል። ይህንንም ለመላው ዓለም በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል። መለስ ግን ከሥልጣኑ በሰላም ለመወርድ አሻፈረኝ ብሏል። የሕዝቡን ድምፅ በመስረቅ በሥልጠን ለመቀጠል የሚያደረግውን ህገ ወጥ ድርጊት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ የወጣውን ዜጋ በአደባባይ በመረሸንና በማቁሰል፥ ቁጥሩ ያልታወቀውንም ዜጋ ወደ ወኅኔ ቤቶች መክተቱን እያወቁ፥ ምዕራባውያን የበላይ ጠባቂዎቹም፥ ከአምባገነኑ ሥርዓት ጎን በመቆም የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ጥያቄ ትግል ለማፈን ተባብረዋል። ይህንን ለማድረግ የተገደዱት፥ ኢትዮጵያን በምንም መንገድ መልቀቅ የለብንም ከሚል የተሳሳተ ድምዳሜ በመድረሳቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚተዳደርበት የፖሊቲካ አመራር፥ በውጭ ኃይል ሲወድቅ ከማየትስ የበለጠ ምን የቅኝ ተገዥነት ሊኖር ይችላል? ራሱን ነፃ ያላወጣ መሪ፥ ሰብዕናውን ከቀኝ ተገዥነት ሥነ ልቦና ያላላቀቀ ቡድን፥ እንዴትስ ኢትዮጵያን ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ነፃ ሊያወጣ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል?

በአሁኑ ወቅት መለስና ግብረ-አበሮቹ በሦስት ኃይሎች ተወጥረው-ተቀስፈው ተይዘዋል። የመጀመሪያው ረድፍ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መራራና ኃያል ትግል ነው። በሁለተኛው ደረጃ ደግሞ የሀገሪቱ ሁለንተናዊ ሁኔታ፥ ማለትም የፖሊቲካው ውጥረትና ግለት፥ የኢኮኖሚው መንኮታኮትና የማኅበረሰባዊው ቀውስ ሲሆን፥ በሦስተኛው ረድፍ ደግሞ የምዕራብያኑ ተፅዕኖና መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይታረቅ የሚያድርጉት ግፊትና ዕኩይ ምክር ነው። ይህ እንደ ቆሰለ አውሬ የተቅበዘበዘና እንደ ተከበበ ጦር ዙሪያው ገደል የሆነበት ያገዛዝ ቡድን፥ ከዚህ ጭንቀት ለመወጣትና ብሎም፥ለጊዜ መግዣ ይረዳኛል ብሎ የሚገምተው፥ እንዳለፈው ጊዜ የሕዝቡን የትግል አቅጠጫና ትኩረት ለማደናገር መሞከር ነው። አሁንም እንደ ትላንቱ የጦርነት አዋጅ በማወጅ፥ የክተት ነጋሪት በማስጎሰምና የእሳት አዳጋ ነዲድ በማቀጣጠል፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የትግል አቅጣጫ ለማስቀየር ሰሞኑን መለስ ዜናዊ፥ የሽብር ፕሮፓጋንዳውን በስፋት ይዞታል። ዛሬም እንደ ትላንቱ፥ “ ከባድመ መለስ' ወደ መለስ” የሚለው መፈክር ይዝልኛል ብሎ ደምድሟል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ ድንበርህ ተጣሰ፥ፀጥታህ ተቃወሰ፥ ነፃነትህ ተደመሰሰ፥ ሉዋላዊነትህ ተደፈረ፥ አንድነትህ ተናጋ፥ ወዘተ በማለት፥ ለሌላ ዙር ዕልቂት እንዲዘጋጅ የሥነ ልቦና ልፈፋውን ጀምሯል። ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች ለመዘመናት አብረው ኖሩ እንጅ በጠላትነት ተፋራርጀው በጦር ሜዳ የተላለቁበት ታሪክ ተመዝግቦ አልቆየነም። በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት፥ ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች፥አብሮ ተባብሮ ከመኖር በስተቀር፥ ጦር የሚያማዝዛቸው አንዳችም ምክንያት አለ ብሎ አያምንም። ሰው ሰራሽ ድንበር በመካለል፥ ወይም የባህር በር ሄደ መጣ ብለው ሁለቱም ሕዝቦች መተላለቅ አለብን ብለው እንደማያምኑ፥ ነግ ከነገ ወዲያ

ታሪክ የሚመሰክረው ሀቅ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባዕድ ወራሪ ኃይል ለዘመናት የተወጋና ድባቅ እየመታ የመለሰ መሆኑ ባይካድም፥ የኤርትራ ሕዝብ እንደ ባዕድ ጠላት በመምጣት ይወርረኛል ብሎ ለማመን ያዳግተዋል፡፡ በአምነባገነኖች የፖሊቲካ ክስረትና ውድቀት መንስዔ ሁለቱ ወንድማማቾች እንደጋና ለሌላ ዙር ጦርነት ሰለባ በመሆን መተላለቅ የለባቸውም፡፡ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደገና ወደ ጦር እሳት ለመማገድ የሚያደርጉትን ሙከራ፥ ሁሉም ዜጋ እንደትላንቱ በእንዝህላልነት ሊመለከተው የሚገባ አይሆንም፡፡ ገዥዎች በሚጭሩት የጦርነት እሳት ሕዝባችን የሚርመጠመጥበት ምክንያት ጭራሽ አይታየውም፡፡ ገና ለገና መለስን ለሌላ አምስት ዓመት በሥልጣን ለማቆየት ሲባል፥ የእለት ጉርስ፥ የዓመት ልብስ የሌለው ድሃ ሕዝባችን ለዳግም የጦርነት ዕልቂት ማገዶ እንዲሆን ሊፈረድበት ይገባል ብሎ መወሰን፥ ታላቅ ብሔራዊ ወንጀል መሆኑን መለስና ተባባሪዎቹ ሊያውቁት ይገባል፡፡

ዕርግጥ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ጉዳይ፥ ማለትም ፖለቲካው፥ ኢኮኖሚው፥ የውጭ ፖሊሲውና ፀጥታው በቀጥታ በውጭ ሀገር መንግሥታት አቅጣጫ ሰጭነትና ትዕዛዝ የሚመራ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፥ የመለስ ዜናዊ የአሁኑ የጦር ነጋሪት መጎሰም የባዕዳን ምክር የለበትም ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ ይህም ክስተት ሁለት ዓላማን ለማስፈፀም ይረዳ ይሆናል ብለው የሚያምኑ የፖሊተካ ታዛቢዎች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ አንደኛው፥ ምዕራባውያኑ፥ በዚህ ሊመጣ በሚችለው ጦርነት ሳቢያ፥ የጦር መሳሪያ ሽያጫቸውን ለማጧጧፍ ዕድል ለመግኘት ሲችሉ፥ ሁለተኛው ስሌታቸው ደግሞ፥ የወደዱትን ግለሰብ በሥልጣን ለማቆየት ያስቸለናል ስለሚሉና የሚጠሉትን ደግሞ ለማስወገድ ምክንያት እናገኛለን ብለው ስለሚመኙ ነው፡፡ የዚህም አንደምታ፥ ምዕረባውያኑ አካባቢውን ላልተወሰነ ጊዜ ለመቆጣጠር ሲሹት የነበረውን ፍላጎት ያሳካልናል ብለው ይመኛሉ፡፡ አንዱ በሥልጣን ቆየ፥ ሌላው ተወገደ፥ ዞሮ ዞሮ በዚህ ጦርነት ተጎጅ የሚሆኑት ሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች መሆናቸው ግን የሚካድ አይሆንም፡፡ ይህ ሁለተኛው ዙር ጦርነት ከተጀመረ፥ ከመጀመሪያው የበለጠ አሰቃቂና አውዳሚ እንደሚሆን ሁሉም የፖሊቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል፡፡ በዚህ እልህ አስጨራሽ በሚሆነው ጦርነት ምክንያት ያካባቢው የሰላም የመረጋጋትና የፀጥታ ሁኔታ ማንም ሊቆጣጠረው በማይችል ደረጃ አስከፊ ከመሆኑም በላይ የሚያስከትለው የፖሊቲካ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አንደምታ ቀላል አይሆንም፡፡ ከሚያስከትለው የሕዝብ ዕልቂት ሌላ የሚፈናቀለው ሕዝብና የስደተኛው ብዛት አሃዙን መገመት ያስቸግራል፡፡ በአካባቢው የሚያመጣው የአየር ብክለትና የተፈጥሮ ውድመትም በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፥ በድህነታቸው በዓለም መጨረሻውን ደረጃ የያዙት እነዚህ ያልታደሉ ሕዝቦች፥ በጦርነቱ ምክንያት ኢኮኖሚያቸው ድምጥማጡ እንደሚጠፋ መገመት ነቢይነትን የሚጠይቅ አይደለም፡፡

ይህን ሁሉ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ከተቻለ፥ ይህን የጦርነት መቅሰፍት ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ብሎ ማሰብና መፍተሄውን መፈለግ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነትና ግዴታ እንደሆነ መታወቅ ይገባዋል። ስለሆነም፥

1) የኢትዮጵያ ሕዝብ በመለስ ዜናዊ የአቅጣጫ አስቀያሪ ፕሮፓጋንዳ ሳይዘናጋ፥ የጀመረውን የነፃነት ትግል ማፋፋም አለበት።

2) ለውጊያ ተዘጋጅ የሚለው የመለስ ዜናዊ የጦርነት ነጋሪት ጎሰማ፥ አሁን ካለበት የፖሊቲካ አጣብቂኝ ወጥቶ ሥልጣኑን ለማደላደል የሚጠቀምበት ርካሽ ፕሮፓጋንዳ መሆኑን በመረዳት፥ ከጦርነት ይልቅ ሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች በዘለቂታ መልኩ በሰላም የሚኖሩበትን መንገድ መፈለግና መፍተሄውን አግኝቶ በተግባር የሚፈፀምበትን ሂደት ባስቸኳይ መጀመር ይዋል ይደር የሚባል አይደለም።

3) ለዚህም የመጀመሪያው በር ከፋች ሊሆን የሚችለው መጀመሪያ በኢትዮጵያ የሠላምና የዕርቅ ብሔራዊ ጉባዔ ጠርቶ፥ ሁሉንም ወገን ያካተተ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መቋቋም፥ በዚህም ሂደት የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ እንደሆነ ማወቅ፥

4) በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያለው ችግር ሊፈታ የሚችለው በውይይትና በሠላም እንጅ፥ ሁለቱንም ሕዝቦች በሚያወድም ጦርነት ምንም ዓይነት ዘላቂ መፍተሄ እንደማይገኝ ማወቅ፥ ይህንም ሀቅ የኤርትራ መሪዎች ተገንዝበው፥ ኢትዮጵያን ከሚወክል መንግሥት ጋር ባስቸኳይ ውይይት ከመጀመር ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ሊረዱት ይገባል። ይህን ሀቅ ካልተቀበሉ፥ በታሪክና በትውልድ ብቻ ሳይሆን፥ ለሚያስከትለው ሰበብ ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ ልናሳስባቸው እንወዳለን።

5) የኢትዮጵያ ኅብረትስብ ከፍል ጦረነቱ እንዳይጀመር አስፈላጊውን የመከላከል ብለኃት መፈለግ ይገባዋል።

6) በወያኔ ፓርልማ ላለመግባት ያሉወሰኑት የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ ያላቸውን ልዩነት በማስወገድና የኃይል አሰላለፈቸውን በማስተካከል፥ በኅብረት ሆነው ሀገራቸውን ከጥፋት የሚያድኑበትን ዘዴ በአስቸኳይ መፈለግና የብሄራዊ አንድነት መንግሥት የሚመሠረትበንትን ሁኔታ ለመምጣት፥የጋራ ትግላቸውን ማፋፋም፥ በአሁኑ ጊዜ ሀገርን ከጥፋት ከማዳን የበለጠ ሌላ ብሔራዊ የትግል አጀንዳ ሊኖር አይችልም።

7) የዓለም አቀፍ ኅብረተስብ፥ የጦርነቱን አደጋ ለመከላከል የተቻለውን ሁሉ እንዲያደረግ አስቸኳይ ጥሪ ማስተላለፍ፥

8) የኢትዮጵያና የኤርትራ ሠራዊት በዚህ ወንድማማች ሕዝቦችን ለማውደም ለሚጠራው የእርስ በእርስ ጦርነት መለሽ ሳይሰጡ÷ ዘላቂው መፍተሄ በሰላም እንጅ በጦርነት እንደማይገኝ መረዳት ይኖርባቸዋል። ይህን ካላደረጉ÷ የጠርነቱ ሰለባ የሚሆነው ሕዝባቸው ንፁህ ደም ይፋረዳቸዋል።

9) አምባገነን መሪዎች ይመጣሉ ይጠፋሉም÷ የኢትዮጵያና የኤርትራና ወንድማማች ሕዝቦች ግን አብረው በሠላም እንደሚኖሩ አንጠራጠርም። ይህ ዕውን የሚሆነው ግን በጦርነት አይደለም።

10) ጦርነት አጥፊና አውዳሚ ነው። በጦርነት ያደገ÷ የለማ÷ የበለፀገና የሠለጠነ ሀገር እስካሁን አልተሰማም/ አልታየምም። በመሆኑም÷ ሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች ጦርነቱ እንዳይመጣ እየተከላከሉ÷ ለሠላምና ለዕድገት አብረው የሚተባበሩበትን መንገድ እንዲፈልጉ ጥሪያችንን እናሰማለን።